# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ...... i

ማጠቃለያ (Executive summary):- ...... 1

ክፍል አንድ ...... 4

መግቢያ ...... 4

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ራዕይ፣ አላማ፣ ሥልጣንና ተግባር ...... 5

ራዕይ ...... 5

የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ...... 6

ድርጅታዊ መዋቅር ...... 6

የሰው ኃይል ...... 6

የአገልግሎቱ የፋይናንስ ምንጭ ...... 7

የኦዲቱ ዓላማ ...... 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ...... 7

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫና የመመዘኛ መስፈርት ...... 8

የትኩረት አቅጣጫ ...... 8

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ...... 8

የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ...... 9

የሥራ ሒደት መግለጫ (Process description) ...... 9

ክፍል ሁለት ...... 11

የኦዲት ግኝቶች ...... 11

2.1 በአገልግሎቱ የሚከናወኑ የማዕቀፍ ግዥዎች የኮንትራት ውል አፈጻጸምን በቁጠባ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን በተመለከተ፣ ...... 11

አገልግሎቱ የአሸናፊ ድርጅቶች የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግም ስለመሆኑ፣ ...... 11

አገልግሎቱ አቅራቢዎች የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት በቂ አቅም ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ፣ ...... 12

አገልግሎቱ ግዥ ለሚፈጸምላቸው ተጠቃሚ መ/ቤቶች ውል ከመግባቱ በፊት የዕቃዎችን የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ ማሳወቁን በተመለከተ ........ 14
አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል ማሳወቁን በተመለከተ ..... 16
በገቡት የማዕቀፍ ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ........ 20
አገልግሎቱ እቃዎችን ለተጠቃሚ መ/ቤቶች በውሉ በተመለከተው ጊዜ በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ የሚያስከፍለውን የጉዳት ካሳ በተመለከተ ........ 20
በማዕቀፍ የግዥ ውል ተካተው ተጠቃሚ መ/ቤቶች ያልገዙዋቸው እቃዎችን በተመለከተ 21
የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ለገዟቸው ዕቃዎች በወቅቱ ክፍያ መፈጸማቸውን በተመለከተ ........ 22
2.2 አገልግሎቱ ከመንግሥት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም ........ 24
አገልግሎቱ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ ........ 24
ክፍል ሶስት ........ 26
የመደምደሚያ ሃሳቦች ........ 26
ክፍል አራት ........ 28
የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 28
አባሪ 1፡ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ድርጅታዊ መዋቅር ........ 30
አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ........ 31
አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ የመንግስት መ/ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና አቅራቢ ድርጅቶች ........ 33

## ማጠቃለያ (Executive summary):-

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈፃፀም ላይ የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006- 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን በማካተት ነው፡፡

በመንግሥት መ/ቤቶች በወል የሚፈለጉ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማካኝነት አጠቃሎ ለመግዛት የሕግ መሠረት እንዲኖራቸው ተሻሽሎ በወጣው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች እና የንብረት ማስወገድን ጨምሮ በኃላፊነት የሚመራ እራሱን የቻለ አካል ማደራጀት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የሚባል ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 184/2002 ሆኖ ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመሆን እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

በመሆኑም አገልግሎቱ ሊፈጽማቸው ሲገባ ያልፈጸማቸው ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አገልግሎቱ ከአሸናፊ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ውሉን ለመፈፀም የሚያስችል የአቅራቢውን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም ግምገማ ቢያደርግም ቅሬታ የቀረበባቸው አቅራቢዎች ላይ የእርምት እርምጃ የማይወስድ ከመሆኑም በላይ፣ በድጋሚ ለ3 ዓመት (2008-2010) የማዕቀፍ ውል ስምምነት እንዲፈፅሙ ማድረጉ፣
- አገልግሎቱ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ናሙና አለመላኩ፣ ተቋማትም ዕቃዎችን የተፈለገውን ጥራት ማሟላቱን በላብራቶር ወይንም በባለሙያ አረጋግጠው የማይረከቡ መሆኑ፣ አገልግሎቱ እቃዎች በሚፈለጉበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት በስፔስፊኬሽን መሰረት በትክክል ገቢ ስለመሆኑ ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ለሚፈፅሙ ለመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች የግዥ ሂደት አጠናቆ ከአቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል እስከ ስድስት ወር ዘግይቶ የሚያሳውቅ መሆኑ እና የመንግስት ተጠቃሚ መ/ቤቶች ውሉን በመጠባበቅ ስራቸውን በተፈለገው ጊዜ እንዳያከናወኑ ተፅዕኖ መፍጠሩ፣

- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በማዕቀፍ ስምምነቱ ውልና በውሉ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን በመከታተል ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ አለማድረጉ፣ በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል በተጠቀሰው መሰረት የግዥ ትዕዛዝ በደረሳቸው በ7 ቀን ውስጥ እቃዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ ያላስከፈለ መሆኑ፣
- ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መፈፀሙን አገልግሎቱ የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣ የሚሉት

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል ስምምነት በተገቢው ጊዜና በተፈለገው ጥራት አቅርቦቱ ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ በአጥጋቢ ሁኔታ ተግባራዊ ካልሆነ በአገሪቱ ውስጥ የላቀና ተመራጭ ተቋም እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አገልግሎቱ ከአሸናፊ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት አቅራቢው ውሉን ለመፈፀም የሚያስችል ብቃት እና የፋይናንስ አቅም ስለመኖሩ ሊያረጋግጥና የአቅራቢውን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ አሸናፊ አቅራቢዎች እናቀርባለን ያሉትን እቃ በሚፈለገው ጥራት መሆኑን ለማረጋገጥ በላብራቶሪ መፈተሽ ያለባቸውን በላብራቶሪ በማስፈተሽ እና ሌሎቹንም በጨረታ በተጠቀሰው ስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎችም እቃዎቹን ሲረከቡ በስፔሲፊኬሽን በተገለፀው መሰረት የቀረበ መሆኑን በላብራቶሪና በባለሙያ በማረጋገጥ ሊረከቡ ይገባል፡፡ አገልግሎቱም መስፈርት በማዘጋጀት እና መርሃ ግብር በማውጣት የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን በሚፈልግበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት እንዲሁም በስፔስፊኬሽኑ መሰረት በትክክል ገቢ

ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥበት እና የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

- አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ለሚፈፅሙ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ከአቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል በየበጀት አመቱ መጀመሪያ መላክ እና ለተጠቃሚ አካላት መድረሱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች የማዕቀፍ ስምምነት ውልና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን ክትትል በማድረግ ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ሊያደርግና በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ እርምጃ የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል በተጠቀሰው መሰረት የግዥ ትዕዛዝ በደረሳቸው በ7 ቀን ውስጥ እቃዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ ማስከፈል አለበት፡፡
- ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ለዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በውሉ መሰረት በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መፈፀሙን አገልግሎቱ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. መንግሥት በየዓመቱ ከሚመድበው በጀት ውስጥ እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው ለግዥ የሚውል ነው፡፡ የግዥ አፈፃፀም ውጤታማነት የሚለካው ፍላጎትን ለሟሟላት ወጪ ለተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግሥት ሀብት የሚፈስበት የመንግሥት ግዥ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙ አዝጋሚና ለብክነት የተጋለጠ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለግዢ ሥራ የሚመደቡ ባለሙያዎችም በቂ የትምህርት ዝግጅት የሌላቸውና በልምድ ብቻ የሚሠሩ የነበሩ በመሆናቸው እና ንብረት ማስወገድንም በተመለከተ ጥቅም ላይ የማይውል የመንግሥት ንብረት በተገቢው ጊዜ የማስወገድ ባህል በአገራችን የተለመደ አልነበረም፡፡ በዚሁ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቶች ይዞታ ሥር የሚገኙ ንብረቶች ለአገልግሎት በማይፈለጉበት ጊዜ በወቅቱ ስለማይወገዱ ለዝናብና ፀሐይ ተጋልጠው በሚደርስባቸው እንግልት ዋጋቸው እየቀነሰ መንግሥት ከንብረቶቹ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም የሚያጣ ከመሆኑም በላይ ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚገባውን ቦታ ጨምሮ በመያዝ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል፡፡

2. ስለሆነም ለመንግሥት ግዥ ለተከፈለ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም መገኘቱን ለማረጋገጥ፣ የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን የበለጠ ሀብትና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ግልጽ አሠራርን መሠረት አድርጎ በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችሉ አደረጃጀቶች እንዲኖሩት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3. በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ረገድ በተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምን ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ይጠቅማሉ ተብሎ የታመነባቸው የጥናቱ ሀሣቦች የሕግ መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተሻሽሎ በወጣው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ከተካተቱ ለውጦች መካከል አንደኛው በመንግሥት መ/ቤቶች በወል የሚፈለጉ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማካኝነት አጠቃሎ መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ተደንግጓል፡፡

4. በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች እና የንብረት ማስወገድን ጨምሮ በኃላፊነት የሚመራ እራሱን የቻለ አካል ማደራጀት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የሚባል ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 184/2002 ሆኖ ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመሆን እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ራዕይ፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

**ራዕይ**

5. በአገሪቱ ውስጥ የላቀና ተመራጭ የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሰጭ ተቋም መሆን፣

**ዓላማ**

6. አገልግሎቱ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡

1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ በተገቢው ጊዜና በተፈላጊው ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል፣

2) በሽያጭ እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረቶች በተቀላጠፈ አኳኋን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲወገዱ ማስቻል እና

3) ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዕቃና አገልግሎት ግዢ እንዲሁም በንብረት ማስወገድ ረገድ እገዛ ማድረግ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

**ሥልጣንና ተግባር**

7. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 184/2002 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-

ሀ/ ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ የሚወሰን የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና

አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤

ለ/ ግምታቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት ሥር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፣

ሐ/ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግሥታት እና ለግሉ ዘርፍ፤

1) በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሠረተ የአገር ውስጥና የአለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶች ይሰጣል፣
2) የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልገሎት ይሰጣል፡፡

መ/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፡፡

ሠ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

ረ/ ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማች ተግባሮችን ያከንውናል፣

የሚሉ ናቸው፡

## የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

8. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኖ በስራ አመራር ቦርድ የሚተዳደር ሲሆን በአንድ ዋና ዳይሬክተር፣ በሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና በአስር የስራ ሂደቶች ተዋቅሯል:: ለዋና ዳይሬክተር ተጠሪ የሆኑ ስድስት የስራ ሂደቶች ያሉ ሲሆን አራቱ የስራ ሂደቶች በሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚመሩ ናቸው፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

9. አገልግሎቱ በ2002 ዓ.ም በፀደቀው መዋቅር መሠረት ክፍት የስራ መደቡን ጨምሮ 245 ሲሆን እስከ ታህሳስ /2009 ዓ.ም ድረስ ወንድ 79 እና ሴት 80 ሰራተኛ

በድምሩ 159 ሰራተኛ በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ የነዚህ ሰራተኞች በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ማስተርስ 13፣ በመጀመሪያ ዲግሪ 90፣ ኤል ኤል ቢ 4፣ ዲፕሎማ 20፣ ቴክኒካል ዲፕሎማ 4፣ ከ10 እስከ 12ኛ ክፍል 19 እንዲሁም ከ10ኛ ክፍል በታች 9 ናቸው ፡፡

## የአገልግሎቱ የፋይናንስ ምንጭ

10. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለሰራተኞች ደመወዝና ለሚያከናውናቸው ስራዎች ወጪ መሸፈኛ የሚሆነውን ገንዘብ ዋና ምንጩ በየበጀት ዓመቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር የሚመደብለት በጀት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ2006 እስከ 2009 የመጀሪያው ሩብ ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና ያወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው | | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመብለጥ | በማነስ | |
| 2006 | 800,905,363.15 | 800,112,556.90 | - | 795,806.25 | 99.9% |
| 2007 | 17,007,702.00 | 16,344,388.27 | - | 663,313.73 | 96.1% |
| 2008 | 241,781,654.43 | 228,865,941.01 | - | 12,915,713.42 | 94.6% |
| 2009 (1ኛ ሩብ አመት) | 7,800,554.81 | 4,406,822.13 | | | |

## የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፣ የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት እና በቅንጅት የሚተዳደሩ ውሎች የኮንትራት ውል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በተገቢው ጊዜና በተፈለገው ጥራት አቅርቦቱ ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ መፈፀሙን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ ሲሆን፤ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አጥጋቢ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈጻጸምን

በተመለከተ ለመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚያስረክብበት ሥርዓት ብቃት ያለው ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫና የመመዘኛ መስፈርት

### የትኩረት አቅጣጫ

13. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም፦

I. በአገልግሎቱ የሚከናወኑ የማዕቀፍ ግዥዎች የኮንትራት ውሎች አስፈላጊ የሚባሉ የእቃ መግለጫዎች፣ በስፔስፍኬሽን፣ በናሙና በሚፈለገው መጠን፣ እና ጊዜ ለመንግስት መሥሪያ ቤቶች ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚረከቡበት የአሰራር ስርዓትን መገምገም፣

II. አገልግሎቱ ከመንግሥት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

14. ከላይ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 16 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተቋቋመበት ደንብ፣ የሥራ መመሪያ እና በአገልግሎቱ የተጠናው ውጤት ተኮር የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናት፣ ሚዛናዊ ዉጤት ተኮር ሥርዓት (BSC)፣ ከ2003-2007 እና ከ2008-2012 የተዘጋጁ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዶች፣ ከ2006-2008 እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የቦርድ ቃለ-ጉባዔ እና ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ የማዕቀፍ ውል ስምምነት ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ለአገልግሎቱ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

15. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2006 እስከ 2009 የመጀመሪያው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

16. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሲሆን በተጨማሪም 8 የመንግስት መ/ቤቶች፣ 4 ዩኒቨርሲቲዎችና በስራቸው የሚገኙ 5 ኮሌጆች እንዲሁም 5 አቅራቢ ድርጅቶችን በናሙና በመምረጥ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበው ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የመንግስት መ/ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና በሥራቸው የሚገኙ ኮሌጆች እንዲሁም አቅራቢ ድርጅቶች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

## የሥራ ሒደት መግለጫ (Process description)

17. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈፃፀምን አስመልክቶ የዘረጋው የአሰራር ሒደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የውል አስተዳደር የስራ ሒደት**

- ለማዕቀፍ ስምምነት ውሎች በመጀመሪያ የውል ማስከበሪያ መያዙን ያረጋግጣል፣ እቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶችንና የሚቀርቡትን የእቃ አይነት በመለየት መጠኑንና ጠቅላላ ዋጋ የሚገልጽ መረጃ ይሰበስባል፡፡
- ከተጠቃሚ ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመሰብሰብ፣ በቂ የእቃ አቅርቦት ያላቸውን ድርጅቶች፣ እንዲሁም እቃዎችን ተረክበው ክፍያ ያልፈጸሙ ባለበጀት መስሪያ ቤቶችን በማጣራት ይለያል፡፡ የአቅራቢ ምደባ ለውጥ ጥያቄዎችን አግባብነት ተመልክቶ ተለዋጭ አቅራቢ ድርጅቶች እንዲመረጡ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ተለዋጭ አቅራቢ ድርጅቶችን በደብዳቤ ያሳውቃል አፈጻፀሙን በመከታተል ክፍያ ላልፈጸሙ ተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች ካሉ ለበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

- ለውል አስተዳደር ስራዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ሃገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውንና የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችንና አገልግሎቶችን የግዥ ረቂቅ ውል ያዘጋጃል፡፡ በረቂቅ ውሉ ላይ ከአሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ተወያይቶ ስምምነት ላይ ይደርሳል፡፡ በመቀጠል የውል ሰነዶች እንዲፈረሙ ያደርጋል፡፡ አቅራቢዎች በግዥ መመሪያው መሰረት ያቀረቡትን የውል ማስከበሪያ ዋስትና በመያዝ ያስተዳድራል የመተማመኛ ሰነድ (Letter of Credit) ማሻሻያ ጥያቄዎችን ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል፣ የውል አፈጻጸም ልዩነት ሲያጋጥም የውል ማሻሻዎችና የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሃሳብ ያቀርባል፣ በውሉ መሰረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑንና ለተከፈሉ ክፍያዎች ተገቢው አገልግሎት መገኘቱን ይከታተላል ግብረመልስ ይሰጣል፡፡ ከሶስተኛ ወገኖች ማለትም ከኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ ከአጓጓዥ ድርጅቶች፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከጉምሩክና ዕቃ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የአገልግሎቱ ጥቅሞች መከበራቸውንና የአገልግሎቱ ግዴታዎች የተፈጸሙ መሆናቸዉን ክትትል ያደርጋል፡፡
- አቅራቢ ድርጅቶች በውሉ መሰረት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችንና አገልግሎቶችን ካላቀረቡ በውሉ መሰረት ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ ድርጅቶች ዕቃዎችን ውሉ ላይ በተቀመጠው ጊዜና ጥራት መሰረት እያቀረቡ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የማዕቀፍ ስምምነቱ ሲጠናቀቅ የውል አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ የውል ማስከበሪያው እንዲለቀቅ ክትትል ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 በአገልግሎቱ የሚከናወኑ የማዕቀፍ ግዥዎች የኮንትራት ውል አፈጻጸምን በቁጠባ፤ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን በተመለከተ፤

**አገልግሎቱ የአሸናፊ ድርጅቶችን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግም ስለመሆኑ፣**

18. አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

19. በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ እቃ ለማቅረብ ጨረታውን የአሸነፉትን አቅራቢዎች ከመወሰኑ እና ከአሸናፊ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት የአቅራቢዎችን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቷል፡፡ ነገር ግን የተዘረጋው ሥርዓት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ውስጥ አንዳንድ አቅራቢ ድርጅት በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ ከማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ቅሬታ ቢቀርብም አገልግሎቱ በውሉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ ሲሆን ይልቁንም በድጋሚ ለ3 ዓመት (2008- 2010) የማዕቀፍ ውል ስምምነት ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

20. ለማሳያ ያህል፡- በ2007 በጀት ዓመት፣

- ማፍ ኢንተርናሽናል የአቅርቦት ድርሻ 20 በመቶ የሆነውን ኤ ፎር ሀርድ ከቨር ፔፐር፣ ትራንስፓራንሲ (ፕላስቲክ)፣ ማስታወሻ ደብተር ትልቁ ፣ ቦክስ ፋይል እቃዎችን ያላቀረበ መሆኑ፤
- አባድር ሾፒንግ ሴንተር ኃ/የ/የግል ማህበር የአቅርቦት ድርሻ 100 በመቶ የእጅ መታጠቢያ ሳሙና (ብቸኛ አቅራቢ) ሲሆን እቃዎችን እያቀረበ አለመሆኑን፣
- ባሰፋ ትሬዲንግ vehicle tyre 11.00 R20 with inner tube & flap የአቅርቦት ድርሻ 100 በመቶ ቢሆንም እቃዎቹን ያላቀረበ መሆኑን፤

- ባሰፋ ትሬዲንግ vehicle tyre 12.00 R20 with inner tube & flap የአቅርቦት ድርሻ 60 በመቶ ቢሆንም እቃዎችን ያላቀረበ መሆኑን፤
- እንዲሁም የካቲት የወረቀት ስራዎች ኃ/የተ/የ/ማ ማስታወሻ ደብተር የአቅርቦት ድርሻ 20 በመቶ ሲሆን እቃዎችን እያቀረበ አለመሆኑን፣

የውል አስተዳደር የስራ ሒደት የ2007 በጀት ዓመት የማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

21. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት በዋነኛነት በአቅራቢዎች ላይ እንደ አገር የአቅም ውስንነት ችግር በመሆኑ ሁሉንም ሊያሟላ የሚችል አቅራቢ አይኖርም፡፡ ስለሆነም መጠነኛ ግድፈት ቢኖርባቸውም ሥራው እንዳይቆም በሚል እሳቤ ውል የሚፈርሙ አቅራቢዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ ካልሆነ አገልግሎቱ ምንም ግዢ መፈፀም አይችልም በሚል ሥጋት አንዳንድ አስቸጋሪ አቅራቢዎችን ለመሸከም መገደዳቸውን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የፋይናንስና የማቅረብ አቅማቸው (ከሚገዛው ከ20 ከመቶ እስከ መቶ ፐርሰንት ለመስጠት) ከመጀመሪያው ተገምግሞ አሸናፊ ማድረግ ይገባ ስለነበረ እና የሚቀጥለውን ጨረታ አሸናፊ ሲያደርግ ያለፈውን አፈጻጸም ከግምት አለማስገባቱ መጠነኛ ግድፈት አለባቸው የተባለው አሳማኝ ምላሽ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

22. አገልግሎቱ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ተፈራርሞ በውሉ መሰረት ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ዕቃዎቹን በውሉ መሰረት ባለማቅረባቸው በመንግስት ሥራ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በተጨማሪም ቅሬታ የቀረበባቸውና የገቡትን የውል ስምምነት ካልተወጡት አቅራቢዎች ጋር በድጋሚ ለ3 ዓመት (2008- 2010) የማዕቀፍ ውል ስምምነት መፈፀሙ ባለፈው የተከሰቱት ችግሮች ወደፊትም እንዲቀጥሉ በማድረግ በመንግስት ሥራ ላይ ማጓተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

**አገልግሎቱ አቅራቢዎች የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት በቂ አቅም ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ፣**

23. አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ የሚፈለጉ ዕቃዎችን ለማቅረብ ተወዳድረው ጨረታ ያሸነፉ አቅራቢዎች ጋር የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት አሸናፊዎቹ ለማቅረብ የተወዳደሩትን እቃዎች በተፈለገው ጥራት፣ ጊዜና፣ መጠን ወዲያውኑ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ አቅም (ክምችትን ጨምሮ) ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

አቅራቢዎቹም በውሉ መሰረት በተፈለገው ጊዜ፣ መጠንና ጥራት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

24. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ የመንግስት መ/ቤቶች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና የግዥ ባለሙያዎች በሰጡት መልስ በግዥ ትዕዛዝ (purchase order) የጠየቁት እቃ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እየቀረበላቸው እንዳልሆነ፣ በማዕቀፍ ዕቃዎችን ለማቅረብ ጨረታ ከአሸነፉት አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ በናሙና ከታዩት አቅራቢዎች ውስጥ አባድር ሾፒንግ ሴንተር ኃ/የተ/የ/ማ(የእጅ ሳሙና) የካቲት ወረቀት ሥራዎች ድርጅት እና አማ ወረቀት እና የወረቀት ማሸጊያ አምራች ኃ/የ/የ/ማ (የፕሪንተር ወረቀት) ጌድ ኃ/የተ/የግ/ማ (ኡሁ) አልታ ኮምፒውተር ኃ/የ/የ/ማ (ኤል ሲዲ ፕሮጀክተር) በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እቃዎችን እያቀረቡ እንዳልሆነ ገልፀዋል ፡፡

25. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የሰጡት አስተያየት የውጭ ምንዛሪ እንደ ልብ የሚገኝበት ሁኔታ ባለመኖሩ ተራ የመጠበቅና ከላይ በተገለፀው የአቅም ማነስ ችግር እንዲሁም ተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዢ ፍላጐታቸውን በትክክል ባለማሳወቅ በተወሰኑ ዕቃዎች ላይ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ውስጥ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡ ነገር ግን በግምገማ ወቅት የተጫራቾች አቅም የሚፈተሽበት "Post qualification" መመዘኛ ሥርዓትን አልፈው እንደሚመጡ መታወቅ ይኖርበታል ብለዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የማዕቀፍ ግዥ ከመከናወኑ በፊት ከሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎት ተሰብስቦ የሚፈለገው ዕቃ መጠን በቅድሚያ ታውቆ ጨረታ መውጣት ስላለበት የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

26. አቅራቢዎች ውል ከመፈፀማቸው በፊት የሚያቀርቡትን እቃ በተፈለገው ጊዜና መጠን ለማቅረብ ብቃታቸው እና አቅማቸው በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥ ውል የሚዋዋል በመሆኑ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች የተቋቋመበትን አላማቸውን በተገቢው መንገድ እንዳያሳኩ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ከፍሎች በተያዘላቸው እቅድ መሰረት የመማር ማስተማር ሒደቱን እንዳያከናውኑ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ ሥራዎችን ለማከናወን ከታቀደው ጊዜ በላይ ሊወስድ እና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

**አገልግሎቱ ግዥ ለሚፈጸምላቸው ተጠቃሚ መ/ቤቶች ውል ከመግባቱ በፊት የዕቃዎችን የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ ማሳወቁን በተመለከተ**

27. አገልግሎቱ ግዥ ለሚፈጸምላቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ለእያንዳንዱ ዕቃ አቅራቢዎቹ እናቀርባለን ያሉትን ዕቃ ጥራት አስቀድሞ በላብራቶሪ መረጋገጥ ያለበትን በላብራቶሪ፣ በባለሙያ መታየት ያለበትን በባለሙያ በማረጋገጥ ይህንኑ የሚያሳይ ናሙና ወይንም በቴክኒክ መግለጫ /specification/ መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን አረጋግጦ ሊልክ ይገባል፡፡ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎችም የሚገዟቸውን ዕቃዎችና ንብረቶች በተላከላቸው ናሙና እና ቴክኒክ መግለጫ /specification/ መሰረት መሆኑን አረጋግጠው ሊረከቡ እና አገልግሎቱም ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

28. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ውል ለተዋዋለላቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የቴክኒክ መግለጫ /specification/ በሲዲ የሚልክ ሲሆን ናሙና ግን እየላከ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ ተጠቃሚ መ/ቤቶች በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ስለመኖሩ በሚጣራበት ጊዜ፡-

- የአገልግሎቱ የ2007 እና የ2008 በጀት ዓመታት እቅድ አፈፃፀም ላይ እቃዎቹ በአግባቡ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች በወቅቱ መድረሳቸውን ያለመከታተልና በሚፈለገው ደረጃ ማስተዳደር አለመቻሉን መገለጹ፣
- አገልግሎቱ አቅራቢዎች ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑን፣
- ተጠቃሚ መ/ቤቶች ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እቃዎች በስተቀር በማዕቀፍ ግዥ የተገዙ እቃዎችን ሲረከቡ በውሉ ላይ በተቀመጠው ስፔስፊኬሽንና ናሙና መሰረት ስለመሆኑ በአገልግሎቱ በአልፎ አልፎ ዘዴ እንኳ የማይረጋገጥ መሆኑን፣

- አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል የተገዙ እቃዎችን በውሉ ላይ በተቀመጠው ስፔስፊኬሽንና ናሙና መሰረት በባለሙያ ተረጋግጠ መረከባቸውን የማረጋገጥ ስራ በዓመታዊ እቅድ በማካተት ያልሰራ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ስምንት የመንግስት መ/ቤቶች፣ አራት ዩኒቨርሲቲዎችና በስራቸው የሚገኙ አምስት ኮሌጆች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና የግዥ ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ አገልግሎቱ ስፔሲፊኬሽኑን በሶፍት ኮፒ (በሲዲ) የሚልክ ሲሆን ናሙና ማየት ለሚያስፈልጋቸው እቃዎች ግን ወደ አገልግሎቱ በመሔድ ትክክለኛነቱን እንደሚያረጋግጡ፣ እንዲሁም እቃዎችን ሲረከቡ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን በባለሙያዎቻቸው አስፈትሸው የሚረከቡ ሲሆን ሌሎች እቃዎችን ሳያስፈትሹ እንደሚረከቡ ገልጸዋል፡፡

30. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ስፔስፊኬሽኑን እንልካለን፣ ናሙና ማየት የሚያስፈልጋቸውን እቃዎች አገልግሎቱ ድረስ መጥተው እንዲያዩ ይደረጋል፣ አገልግሎቱ የሚረከበውን የዕቃዎች ናሙና ትክክለኝነት ለተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ በመላክ ጥራቱን እንደሚያረጋግጡ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከሚገዙት ዕቃዎች አይነት መብዛት አንፃር ናሙና ለሁሉም የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች መላክ አስቸጋሪ እና ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ በመሆኑ ይህንን እንዳላደረጉ ገልጸዋል፡፡

31. በተጨማሪም አገልግሎቱ የሚያደርገውን ክትትል በተመለከተ ተጠቃሚ መ/ቤቶች በውሉ መሰረት የዕቃውን ጥራት፣ የማቅረቢያ ጊዜ እና መጠን ባለሙያዎቻቸውን ይዘው እንዲረከቡ የሚደረግ ሲሆን ተጠቃሚ መ/ቤቶች ሲጠይቁ ለኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፣ ፎቶ ኮፒ፣ ፋክስ ማሽን ስካነር ወ.ዘ.ተ ከአገልግሎቱ የአይቲ ባለሙያዎች ይላካሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉንም ተጠቃሚ መ/ቤቶች መከታተል ስለማይችል በፍላጎት መግለጫው መሠረት እንዲረከቡ ከማሳሰብ ውጪ በክትትል ለማዳረስ በጣም አስቸጋሪ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መስፈርት በማውጣት እና መርሃ ግብር በማዘጋጀት የተወሰኑ መ/ቤቶች ላይ ክትትል ማድረግ ይቻል ስለነበረ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

32. አገልግሎቱ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ናሙና አለመላኩ፣ ተቋማትም ዕቃዎችን የተፈለገውን ጥራት ማሟላቱን በላብራቶሪ ወይንም በባለሙያ አረጋግጠው አለመረከባቸው እንዲሁም መንግስት ዕቃዎቹን ለመግዛት በሚያወጣው ገንዘብ ተፈላጊውን ጥቅም እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ እንዲቀርብና እንዲገዛ በማድረግ ለብልሹ አሰራር በር በመክፈት የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንዲባክን በር ይከፍታል፡፡ እቃዎች በሚፈለጉበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት በስፔስፊኬሽን መሰረት በትክክል ገቢ ስለመሆናቸው ክትትል አለማድረጉ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ሊቀርብላቸው የሚገቡ እቃዎችን በመጠባበቅ ስራቸውን በተቀላጠፈ መልኩ እንዳይሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡ እንዲሁም ሥራው እንዳይቋረጥ ለማድረግ ሲባል አላስፈላጊ ለሆነ ወጪ እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡

**አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል ማሳወቁን በተመለከተ**

33. አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል በወቅቱ ለሁሉም የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ ሁሉም የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች በውሉ መሰረት አስፈላጊውን ግዥ ሊፈጽሙ ይገባል፡፡

34. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል ለሚመለከታቸው ተጠቃሚ መ/ቤቶች ለማሳወቅ እስከ ስድስት ወር ድረስ የሚዘገይ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል እንዲያውቁት የሚያደርግ መሆኑን ነገር ግን እስከ 6 ወር ድረስ የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩን፣ በዚህም ምክንያት የግዥ ሂደቶች የሚፈጸሙት በዋናነት ከበጀት ዓመቱ አጋማሽ በኋላ መሆኑን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና የግዥ ባለሙያዎች ገልፀዋል፡፡

36. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት እና ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን የማዕቀፍ ውል በሀርድ ኮፒና በሲዲ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች የሚልኩ መሆናቸውን፣ ነገር ግን ውሉ የተላከላቸው መ/ቤቶች ስር ያሉ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች የሥራ ክፍሎች ቶሎ ላይደርሳቸው ይችላል፡፡ በዚሁም ምክንያት የውል ማስተዳደር ሥራው የሚጀምረው ውሉ ከተፈረመ በኋላ ስለሆነ የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸው እስከዚያው ድረስ ተጠቃሚ መ/ቤቶች የአቅርቦት ችግር እንዳያጋጥማቸው

ቀድሞ ሲያቀርቡ የነበሩ አቅራቢዎች ውል የማራዘም ስራ ተሰርቷል፡፡ አብዛኛው ችግሩ የተፈጠረው የአንድ አመት ውል ብቻ በመፈረሙ ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ ይህንን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል የ3 አመት ውል እንደተገባ ገልጸዋል፡፡

37. አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ ለሚፈፅሙ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች የግዥ ሂደት አጠናቆ ከአቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል በወቅቱ አለማሳወቁ ለተጠቃሚዎች የእቃዎች አቅርቦት ችግር እንዲያጋጥማቸው እና ስራቸውን በተፈለገው ጊዜ እንዳያከናውኑ ያደርጋል፡፡

**አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች እቃዎችን በወቅቱ ማቅረባቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ**

38. አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) ሲደርሳቸው በስፔስፊኬሽን እና በናሙና መሰረት በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡


39. የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 2 አገልግሎቱ አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል እንዳለበት ቢገለጽም አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) ሲደርሳቸው በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

40. በናሙና ከታዩ የመንግሥት መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች እና የግዥ ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- አቅራቢዎቹ የግዥ ትዕዛዝ ከተሰጣቸው በኋላ የተለያዩ ምክንያቶችን እያስቀመጡ የተፈለገውን ዕቃ በውሉ መሰረት በተገቢው ጊዜና መጠን እያቀረቡ እንዳልሆነ፣
- እስከ ስድስት ወራት እና ከዚያም በላይ ሳያቀርቡ እንደሚያዘገዩ፣ ረጅም ጊዜ ካስጠበቁ በኋላ የለንም የሚሉ አቅራቢዎች እንዳሉ፣ የግዥ ትዕዛዝ ከተቀበሉ በኋላ በምንፈልገው መጠን ሳይሆን አቅራቢዎቹ በሚወስኑት መጠን እንደሚያቀርቡ፣

ገልፀዋል፡፡

41. በዚህም መሰረት ዕቃዎችን ለማቅረብ ጨረታ ከአሸነፉት አቅራቢዎች ውስጥ አባድር ሾፒንግ ሴንተር ኃ/የተ/የ/ማ፤ የካቲት ወረቀት ሥራዎች ድርጅት፣ ጌድ ኃ/የተ/የግ/ማ እና አማ ወረቀት እና የወረቀት ማሽጊያ አምራች ኃ/የ/የ/ማ፣ ኤ ኤስ ኤ ትሬዲንግ፣ ራዲካል ኃ/የ/የ/ማ እቃዎችን ከ19 እስከ 240 ቀናት ሳያቀርቡ እንዳዘገዩ እና በሚፈለገው መጠን እቃዎችን እያቀረቡ እንዳልሆነ ከማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶችና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡




*ግራፍ 1. በናሙና የታዩ የአቅራቢ ድርጅቶች እቃዎችን ሳያስረክቡ ያዘገዩበት ቀናቶች*

42. ይህን በተመለከተ ለየካቲት የወረቀት ስራዎች ማምረቻ ድርጅት፣ ለአማ ወረቀት እና የወረቀት ማሸጊያ አምራች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ለአባድር ሾፒንግ ሴንተር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

- በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት እና ተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች ይዘውት የሚቀርቡት የግዥ ፍላጎት ከአገልግሎቱ ጋር ከተዋዋሉት ውል ላይ ከተገለፀው መጠን ጋር የማይገናኝበት ሁኔታ በመኖሩ፤

- የሚያመርቱት በትዕዛዝ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ የተጠየቁት እቃዎች የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩን፤ ተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች ፍላጎታቸውን በትክክል ስለማያሳወቁ፣ እንዲሁም በአብዛኛው የመንግሥት መ/ቤቶች ፍላጎታቸውን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ስለሚያሳውቁ በውል ከተዋዋሉት በላይ የግዥ ትዕዛዝ ስለሚመጣ፣

መሆኑን ገልጸዋል፡፡

43. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ እና በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ ውል አስተዳደር የሥራ ሂደት በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዢ ትዕዛዝ ለአቅራቢው ሲሰጡ ለአገልግሎቱ በግልባጭ እንዲያሳውቁ በማድረግ አቅርቦቱ በ7 ቀናት ውስጥ መቅረቡን አገልግሎቱ እንደሚከታተል፣ ከአቅራቢዎች ጋር ውል ከተፈራረሙ በኋላ ለመነሻ የማቅረቢያ ጊዜ ከ 60 ቀን ጀምሮ ማቅረብ እንዲችሉ የሚያደርጉ ቢሆንም በውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ በተጠቃሚ መ/ቤቶች ክትትል ማነስ፣ ተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን ለአገልግሎቱ በትክክለኛ መጠንና በወቅቱ አለማሳወቅ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአቅርቦት ላይ ችግር ሲያጋጥማቸው በወቅቱ መፍትሄ እንዲሰጣቸው ለአገልግሎቱ አለማሳወቅ፣ በሌላ በኩል አብዛኛው ግዥ ፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ለአቅራቢዎች የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡት የበጀት ዓመቱ ሊጠናቀቅ አካባቢ መሆኑን፣ ገልፀዋል፡፡

44. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከፈፀመ በኋላ የግዥ ትዕዛዝ (purchase order) ሲደርሳቸው በውሉ መሰረት እቃዎችን በ7 ቀን ውስጥ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ማድረሳቸውን ክትትል የማያደርግ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

45. አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) በደረሳቸው በ 7 ቀን ውስጥ በውሉ መሰረት የሚፈለገውን ዕቃ አለማቅረባቸው እና አገልግሎቱም ተግባራዊነቱን ለመከታተል የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ስራቸውን በተቀላጠፈ መንገድ እና በወቅቱ እንዳያከናውኑ በማድረግ የስራ መስተጓጎል ፈጥሯል፡፡

**በገቡት የማዕቀፍ ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃ በተመለከተ**

46. አገልግሎቱ በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎችን በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

47. በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ ለተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የአቅርቦት ችግር ሲገጥማቸው የአቅራቢ ለውጥ እንዲያደርጉ በደብዳቤ ከማሳወቅና ለአንድ ጊዜ በራሳቸው እንዲገዙ ከማድረግ በስተቀር በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙትን አቅራቢዎች በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

48. የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎችን በተመለከተ አገልግሎቱ በራሱ እርምጃ የሚወስድበት አግባብ አለመኖሩን፣ እንደ አገር ያለው ችግር የአቅራቢዎች አቅም ማነስ በመሆኑ ወደፊት በሂደት እየተስተካከለ ይሄዳል ብለው እንደሚያምኑ ገልፀዋል፡፡ የአገልግሎቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ አገልግሎቱ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በገባው በማዕቀፍ ስምምነቱ ውልና በውሉ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት ያልፈጸሙት ላይ ውሉ ላይ የተቀመጠውን ቅጣት ተግባራዊ አለማድረጉ እና በውሉ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን ክትትል ማድረግ ስለነበረበት የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

49. በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ አገልግሎቱ በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ አለመውሰዱ በማዕቀፍ ውል ሂደት ያሉ ችግሮች እንዳይቀረፉ ሊያደርግ፣ አቅራቢዎች ህግን ተከትለው እንዳያቀርቡ፣ ጥራት የሌላቸው እቃዎች በማቅረብ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማግኘት እንዳይቻል በማድረግ ሥራ እንዲበደል ከማድረጉም በላይ ለህገወጥ አሰራር በር እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

**አገልግሎቱ እቃዎችን ለተጠቃሚ መ/ቤቶች በውሉ በተመለከተው ጊዜ በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ የሚያስከፍለውን የጉዳት ካሳ በተመለከተ**

50. አገልግሎቱ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እቃውን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ በቀረቡት የውል መጠን በየቀኑ 0.1 % የጉዳት ካሳ ሊያስከፍል እና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

51. አገልግሎቱ አቅራቢዎች የግዥ ማዘዣ (purchase order) በደረሳቸው በ7 ቀን ውስጥ እቃውን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ እንደሚከፍሉ በውሉ ላይ General Condition of Contrat (GCC 54.1) የተገለጸ ቢሆንም ከላይ ከተገለጸው ቀን በላይ ባዘገዩ አቅራቢዎች ላይ ክፍያውን እንዲከፍሉ ያልተደረገ እና አስተዳደራዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

52. የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት የመዘግየቱ ችግር ሙሉ በሙሉ በአቅራቢው ጥፋት ብቻ ባለመሆኑ አገልግሎቱ ይህን ቅጣት ለመጣል እንዳልቻለ፣ ቅጣት ላይ ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩ አቅራቢዎች ሊወጡ ይችላሉ ብለው በማሰባቸው ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የአቅራቢ ለውጥ እና ለአንድ ጊዜ ግዥ እንዲፈፅሙ የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መጀመሪያ ጨረታውን ሲያሸንፉ በውሉ መሰረት ለማቅረብ የተስማሙ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

53. አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል በተጠቀሰው መሰረት የግዥ ትዕዛዝ በደረሳቸው በ7 ቀን ውስጥ እቃዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ አለማስከፈሉ አቅራቢዎች በወቅቱ እንዳያቀርቡ ክፍተት ከመፍጠሩ በተጨማሪ መንግስት ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም አሳጥቷል፡፡

**በማዕቀፍ የግዥ ውል ተካተው ተጠቃሚ መ/ቤቶች ያልገዙዋቸው እቃዎችን በተመለከተ**

54. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ለመፈፀም ከአቅራቢዎች ጋር ውል የተዋዋለባቸው እቃዎች በተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎት መሰረት ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተጠቃሚዎች ይገዛሉን ብለው ጠይቀው በጥያቄያቸው መሰረት ካልወሰዱ ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. አገልግሎቱ ከማዕቀፍ እቃ አቅራቢዎች ጋር የተለያዩ ዓይነት እቃዎችን ለማቅረብ በተዋዋሉት ውል እና በጠየቁት ፍላጎት መሰረት አቅራቢዎች እቃዎች ገዝተው በመጋዘናቸው ከተቀመጠ በኋላ የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች የማይገዟቸው እቃዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

56. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃውን ሄደው እንዲረከቡ ከማሳሳብ በስተቀር ኃላፊነት እንደማይወስዱ፣ እርምጃ ለመውሰድ ስልጣኑም ሆነ የማስገደድ ሥርዓቱም እንደሌለ፣ እንዲሁም አገልግሎቱ ለእንዲህ ዓይነት ችግሮች ኃላፊነት እንደማይወስድ በማዕቀፍ ስምምነት ውሉ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠ ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ዕቃዎቹ እንዲገዙ ለማድረግ ጨረታ የሚወጣው እና ከአሸናፊው ጋር ውል ለመግባት መነሻ የሚሆነው ከተጠቃሚዎች የሚመጣው የየአመቱ የግዥ እቅድ በመሆኑ የመጣላቸው የግዥ ዕቅድ በፍላጎትና በበጀት መደገፉን በመጀመሪያ ሊያረጋግጡ ስለሚገባ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

57. አገልግሎቱ ለተጠቃሚዎች ያስፈልጋል ብሎ ጨረታ አውጥቶ ውል ከተፈራረመ በኋላ አሸናፊ አቅራቢዎች እቃዎችን ገዝተው በመጋዘናቸው ካስቀመጡ በኋላ የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች የማይገዟቸው ከሆነ መጀመሪያ ግዢው በእርግጥ በመ/ቤቶቹ የግዥ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ መከናወኑን አጠራጣሪ ከማድረጉ በላይ አቅራቢዎቹን የመስሪያ እና የሥራ ማስኬጃ ካፒታላቸውን በአግባቡ ለመጠቀም እንዳይችሉ በማድረግ ለአላስፈላጊ ወጪ እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡

**የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ለገዟቸው ዕቃዎች በወቅቱ ክፍያ መፈጸማቸውን በተመለከተ**

58. የመንግስት መ/ቤቶች እና የዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ ሊፈጽምላቸው ይገባል፡፡ አገልግሎቱም በገባው ውል መሰረት አቅራቢዎች ላቀረቡት ዕቃ በውሉ መሰረት ክፍያ ስለመከፈሉ አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን ከሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲረከቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ የማይፈጽሙ መሆኑን እና አገልግሎቱም አቅራቢዎች ክፍያ እንዳልተፈፀመላቸው ሲያሳውቁ ብቻ ተጠቃሚ መ/ቤቶችን እንዲከፍሉ በደብዳቤ ከማሳወቅ በስተቀር ክፍያው መፈፀሙን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. እንዲሁም አገልግሎቱ ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ አቅራቢ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ ተጠቃሚ መ/ቤቶች በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ እንዲፈጽሙ በውሉ ላይ General Condition of

Contrat (GCC 34.4) የተገለጸ ቢሆንም በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ የማይፈፀም መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ አገልግሎቱም ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ክፍያ እንዲፈፅሙ በደብዳቤ ከማሳሰብ በስተቀር የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ እና ክፍያ የሚያዘገዩ መ/ቤቶችን በተመለከተ ክፍያ በማዘግየታቸው ስለሚወሰነው ቅጣት በማዕቀፍ ውል ላይ ያልተጠቀሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

61. በናሙና የታዩ ስምንት የመንግሥት መ/ቤቶች፣ አራት ዩኒቨርሲቲዎች እና በሥራቸው የሚገኙ አምስት ኮሌጆች የሥራ ኃላፊዎች እና የግዥ ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ እቃዎች ከቀረቡ በኋላ ክፍያ ለመፈፀም ገቢ የተደረጉ እቃዎች በባለሙያ እስከሚፈተሹ ጉዳዩ የሚመለከተው ፈራሚ አካል እስኪፈርም እና ገቢ ሰነድ ተሰርቶ እስከሚቀረጥ ከ5 ቀናት በላይ እስከ አንድ ወር እንደሚወስድ ገልፀዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እቃዎችን ከተረከቡ በኋላ እስከ 3 ወር እና አንዳንድ ጊዜም ከዚያ በላይ ክፍያ እንደሚያዘገዩ ገልፀዋል፡፡

62. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት አቅራቢ ድርጅቶች እቃዎችን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መከፈሉን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ ከአቅራቢዎች ለአገልግሎቱ ሪፖርት ሲደርስ እቃዎችን ገቢ ላደረጉ ተጠቃሚ መ/ቤቶች በደብዳቤ ማሳሰቢያ ከመስጠት ውጪ ምንም እርምጃ እንዳልተወሰደ፣ እንዲሁም ከ 5 ቀን በላይ ክፍያ ለሚያዘገዩ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ስለሚወሰን ቅጣት ውሉ ላይ የተቀመጠ ነገር የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን ከተረከቡ በኂላ በ5 ቀናት ውስጥ መክፈል እንዳለባቸው አስገዳጅ ሁኔታ ለማስቀመጥ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ አስተያየት እንዲሰጡበት የተላከላቸው መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ቢገልጹም ተዘጋጅቷል የተባለውን ረቂቅ መመሪያ ግን አላቀረቡም፡፡

63. ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ለዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መፈፀሙን አገልግሎቱ አለመከታተሉ ክፍያዎች እንዲዘገዩ በማድረግ የአቅራቢ ድርጅቶችን የመስሪያ ካፒታል እና የስራ ማስኬጃ ከመያዙም በተጨማሪ አቅራቢዎችን ለአላስፈላጊ እንግልት ይዳርጋል፡፡

## 2.2 አገልግሎቱ ከመንግሥት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ መሆኑን፣ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም

**አገልግሎቱ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ**

64. አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ ዙሪያ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና አቅራቢዎች ጋር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ እና የተደራጀ የመረጃ ቋት ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

65. አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ ዙሪያ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ እና የተደራጀ የመረጃ ቋት (Date Base) ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

66. በናሙና ከታዩ ስምንት የመንግሥት መ/ቤቶች፣ አራት ዩኒቨርሲቲዎች እና በሥራቸው የሚገኙ አምስት ኮሌጆች የሥራ ኃላፊዎች እና የግዥ ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ ዙሪያ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ እና የተደራጀ የመረጃ ቋት (Date Base) ሥርዓት የሌለው እና ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና አቅራቢዎች ጋር ከደብዳቤና ከስልክ ውጪ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

67. የአገልግሎቱ የውል አስተዳደር የሥራ ሂደት ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ አለመኖሩን፣ ዳታ ቤዝ ለመዘርጋት በእንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን እና ይህንን በተመለከተ አገልግሎቱ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዳታቤዙ ለመጠቀም የአገልግሎቱ የአይቲ ባለሙያዎች ስልጠና የወሰዱ ሲሆን የቢሮ መለዋወጥ በመኖሩ ምክንያት ስራው እንዳይጀመር እንቅፋት መሆኑን፣ ከዚህ በተጨማሪም የአገልግሎቱ ድረ ገፅ ላይ ኢንፎርሜሽን ከመስጠት ባለፈ መረጃ የመለዋወጥ እና የመቀባበል ስራ እየተሰራ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

68. የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት እንደ አገር የሚዘረጋ ሥርዓት እንጂ በአገልግሎቱ ብቻ የሚፈፀም እንዳልሆነ፣ በአገልግሎቱ አቅም አሠራሩን ለማዘመን ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን

ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ሁሉም መ/ቤት የራሱን መረጃ እንዴት በዘመናዊ መልክ እንደሚያደራጅ፣ እንደሚይዝና እንደሚለዋወጥ ሥርዓት መዘርጋት ያለበት ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ሊሰራ የሚችለው መሰረተ ልማትን የማሟላት ስራ ስለሆነ የሰጡትን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

69. አገልግሎቱ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለመተንተንና ለተጠቃሚም ሆነ ለአቅራቢ ድርጅቶችን በፍጥነት እና በጥራት መረጃዎችን ለማሰራጨት የሚያስችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ ተጠቃሚ መ/ቤቶች እና አቅራቢ ድርጅቶች መረጃ በማግኘት ሥራቸውን በቅድሚያ ለማዘጋጀት እና አገልግሎቱም የሚያስፈልጉት መረጃዎችን በመጠቀም ፈጣንና ቀልጣፋ ውሳኔ ለመስጠት እና የውል አስተዳደር ሥራን በተሻለ ብቃት እንዳያከናውን ያደርገዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

70. በመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈፃፀም የአሰራር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተለት ዋና ዋና ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

- ቅሬታ የቀረበባቸው አቅራቢዎች ላይ የእርምት እርምጃ የማይወስድ እና ወደፊት ችግሩ እንደማይደገም ሳያረጋግጥ በድጋሚ ለ3 ዓመት (2008-2010) የማዕቀፍ ውል ስምምነት ከእነዚሁ አቅራቢዎች ጋር መዋዋሉ፣
- አቅራቢዎች ውል ከመፈፀማቸው በፊት የሚያቀርቡትን እቃ በተፈለገው ጊዜና ፣ መጠን ለማቅረብ ብቃታቸው እና አቅማቸው በበቂ ሁኔታ ሳያረጋገጥ አገልግሎቱ ውል የሚዋዋል መሆኑ፣
- አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ናሙና የማይልክ መሆኑ፣ መ/ቤቶቹም አቅራቢዎቹ ጨረታ ያሸነፉባቸውን እቃዎች ከኤሌክትሮኒክስ ነክ ዕቃዎች በስተቀር በላብራቶር እና በባለሙያ የማያስፈትሹ መሆናቸው ፣ በአገልግሎቱም በኩል ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች /የመንግስት መ/ቤቶች/ እቃዎችን በሚፈልጉበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት በስፔስፊኬሽን መሰረት በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ለሚፈፅሙ ለመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች የግዥ ሂደት አጠናቆ ከአቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል እንደተዋዋለ የማያሳውቅ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) ሲደርሳቸው በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን በመደበኛነት የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በማዕቀፍ ስምምነቱ ውልና በውሉ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን በመከታተል ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ አለማድረጉ፣ በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ እርምጃ

የማይወስድ መሆኑ፣ አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል በተጠቀሰው መሰረት የግዥ ትዕዛዝ በደረሳቸው በ7 ቀን ውስጥ እቃዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ ያላስከፈለ መሆኑ፣

- አቅራቢዎች እቃዎችን ገዝተው በመጋዘናቸው ካስቀመጡ በኋላ የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች የማይገዟቸው እቃዎች መኖራቸው የመስሪያ እና የስራ ማስኬጃ ካፒታላቸውን በአግባቡ ለመጠቀም እንዳይችሉ እንዲሁም ለተጨማሪ የመጋዘን ኪራይ ወጪ መዳረጉ፣
- ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ የማይፈጸምላቸው እና አገልግሎቱም መፈፀሙን አገልግሎቱ የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ክትትል አለማድረጉ፣
- አገልግሎቱ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለመተንተንና ለተጠቃሚም ሆነ ለአቅራቢ ድርጅቶች በፍጥነት እና በጥራት መረጃዎችን ለማሰራጨት የሚያስችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

71. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶችና ችግሮች ለማስወገድ ወይም ለማቃለል ይረዳሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

72. የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈፃፀም የአሰራር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡-


- አገልግሎቱ ከአሸናፊ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት አቅራቢው ውሉን ለመፈፀም የሚያስችል ብቃት እና የፋይናንስ አቅም ስለመኖሩ ሊያረጋግጥና የአቅራቢውን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ አሸናፊ አቅራቢዎች እናቀርባለን ያሉትን እቃ በሚፈለገው ጥራት መሆኑን ለማረጋገጥ በላብራቶሪ መፈተሽ ያለባቸውን በላብራቶሪ በማስፈተሽ እና ሌሎቹንም በጨረታ በተጠቀሰው ስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎችም እቃዎቹን ሲረከቡ በስፔሲፊኬሽን በተገለፀው መሰረት የቀረበ መሆኑን በላብራቶሪና በባለሙያ በማረጋገጥ ሊረከቡ ይገባል፡፡ አገልግሎቱም መስፈርት በማዘጋጀት እና መርሃ ግብር በማውጣት የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን በሚፈልግበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት እንዲሁም በስፔስፊኬሽኑ መሰረት በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥበት እና የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ለሚፈፅሙ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ከአቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል በየበጀት አመቱ መጀመሪያ መላክ እና ለተጠቃሚ አካላት መድረሱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ትዕዛዝ (purchase order) ሲደርሳቸው በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን በመደበኛነት የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች የማዕቀፍ ስምምነት ውልና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን ክትትል በማድረግ ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ሊያደርግና በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ

አቅራቢዎች ላይ እርምጃ የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል በተጠቀሰው መሰረት የግዥ ትዕዛዝ በደረሳቸው በ7 ቀን ውስጥ እቃዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ ማስከፈል አለበት፡፡

- አገልግሎቱ ከአሸናፊ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመዋዋሉ በፊት በመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የሚቀርቡ የግዥ ፍላጎቶች በትክክለኛ የግዥ ፍላጎት በጥናት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ የማዕቀፍ ግዥ ጥያቄ ያቀረቡ መ/ቤቶች ንብረቱን በጠየቁት መሰረት የማይገዙበትን ሁኔታ አጣርቶ ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ለዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በውሉ መሰረት በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መፈፀሙን አገልግሎቱ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለመተንተንና ለተጠቃሚም ሆነ ለአቅራቢ ድርጅቶች በፍጥነት እና በጥራት መረጃዎችን ለማሰራጨት የሚያስችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

73. በመጨረሻም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ የተጠየቁትን መረጃዎች በወቅቱ በማቅረብና ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

## አባሪ 1፡ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች |
|---|---|
| I. በአገልግሎቱ የሚከናወኑ የማዕቀፍ ግዥዎች የኮንትራት ውሎች አስፈላጊ የሚባሉ የእቃ መግለጫዎች፣ በስፔሲፊኬሽን፣ በናሙና በሚፈለገው መጠን፣ እና ጊዜ ለመንግስት መሥሪያ ቤቶች ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚረከቡበት የአሰራር ስርዓትን መገምገም፣ | 1. አገልግሎቱ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2. አገልግሎቱ ለባለበጀት መስሪያ ቤቶች ለውል አፈፃፀም የሚረዱ አስፈላጊ ሰነዶች/ የኮንትራት ውል ሰነድ፤ የአቅራቢው አድራሻ፤ የአከፋፈል ሁኔታ፤ የርክክብ ሁኔታ ወ.ዘ.ተ የሚልክበት የአሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 3. አገልግሎቱ አቅራቢዎች የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት እቃዎች በተፈለገው ጊዜና ፣ መጠን ለማቅረብ በቂ አቅም መኖራቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 4. አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋለውን ውል ለሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |
| | 5. አገልግሎቱ ውል የገባባቸው ንብረቶች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው ስፔስፊኬሽን እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 6. አገልግሎቱ ግዥ ለፈጸመላቸው መ/ቤቶች ከአቅራቢዎች የተቀበለውን ስፔስፊኬሽን እና ናሙና ሊልክ ይገባል፡፡ |
| | 7. አገልግሎቱ አቅራቢዎች ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. የመንግስት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ግዥ የተገዙላቸውን እቃዎች እና ንብረቶች በስፔስፊኬሽንና በናሙናው መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ሊረከቡ ይገባል፡፡ |
| | 9. አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) ሲደርሳቸው በሰፔስፊኬሽን እና በናሙና መሰረት በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 10. በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙትን አቅራቢዎች በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት በወቅቱ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች |
|---|---|
| | 11. አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች እና ለዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መፈፀሙን ሊከታተል ይገባል |
| | 12. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ውሎችን ከተዋዋለ በኋላ አቅራቢዎች በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ማቅረባቸውን በመከታተል ዘግይቶ በማቅረቡ ምክንያት በመ/ቤቱ ስራ ላይ ችግር መፍጠሩ ከታወቀ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |
| | 13. አገልግሎቱ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እቃውን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1 % የጉዳት ካሳ ሊያስከፍል እና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| II. አገልግሎቱ ከመንግሥት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም | 14. አገልግሎቱ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር የመረጃ ልውውጥ፣ ለማድረግ የሚያስችል የተደራጀ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 15. አገልግሎቱ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች (አቅራቢዎች) ያቀረቡትን የዕቃ ዓይነት፣ መጠንና ጠቅላላ ዋጋ የሚገልጽ መረጃ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ |
| | 16. አገልግሎቱ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች አቅርቦትን በተመለከተ ከተጠቃሚ ባለበጀት መ/ቤቶች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መሰብሰብና መለየት ይኖርበታል፡፡ |

# አባሪ 3፡_በናሙና የታዩ የመንግስት መ/ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና አቅራቢ ድርጅቶች

## የመንግስት መ/ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች

1. የትምህርት ሚኒስቴር
2. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
3. የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
4. የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር
5. የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
6. በየካቲት 12 ሆስፒታል
7. በትራንስፖርት ባለስልጣን የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
8. የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
9. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በስሩ የሚገኙ፤
    - የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ህንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢኒስቲትዩት
    - ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
    - የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣
10. የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣
11. ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና  በስሩ የሚገኙ፤
    - ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
    - ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
12. የዲላ ዩኒቨርሲቲ፣

## አቅራቢ ድርጅቶች

13. አባድር ሾፒንግ ሴንተር ኃ/የተ/የ/ማ
14. የካቲት ወረቀት ሥራዎች ድርጅት
15. አማ ወረቀት እና የወረቀት ማሸጊያ አምራች ኃ/የ/የ/ማ
16. ማፍ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር (የወረቀት ሥራ)
17. ጌድ ኃ/የተ/የግ/ማ